በአሁኑ ወቅት ጐልቶ የሚታየውን ሁሉን አቀፍ የማስፈፀም አቅም ችግር ደረጃ በደረጃ መቅረፍ ድህነትን ለማስወገድ እና የክልሉን ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሚሆን ከወዲሁ በመታመኑ፤

**WHERE AS**, it is believed to ensure sustainable development and abolish poverity by alleviating the all rounded capacity building problem, now significantly seen step by step, shall play a significant role of it;

ከዚሁ ጋር በተገናኘ መንገድ በስራ ላይ ተሰማርቶ ለሚገኘው አመራርም ሆነ ባለሙያ የአጭር፣ የመካከለኛና እንደተገቢነቱም የረዥም ጊዜ ትምህርትና ስልጠናዎችን በመስጠትና ለጠቅላላው ማህበረሰብ ደግሞ የጥናት፣ የምርምርና የምክር አገልግሎቶችን በማበርከት በክልሉ ውስጥ በሁሉም ዘርፎች የላቀ ውጤት የሚመዘገብበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHERE AS, to render on-the job training of short, medium and, as deemed as necessary, long term education and trainings of the leader, as well as, the professional, and it is necessary to create fovourable condition to the better result, shall be registered by all aspects in the region; contributing the study,research and counceling services to the whole society;

በተለያዩ የገጠርም ሆነ የከተማ አስተዳደር እርከኖች ተሹመው ወይም ተመድበው ለሚያገለግሉ አመራሮችና ባለሙያዎች በየጊዜው የሚሰጡትን ስልጠናዎችና በዘርፉ የሚካሄዱትን የትምህርት፣የጥናት፣ የምርምር እና የምክር አገልግሎት አሰጣጥ ተግባራት በተቀነባበረና በተደራጀ መንገድ የሚያከናውንና ተጨባጭ ፋይዳቸውን በየጊዜው የሚገመግም የተጠናከረ አካል በአዲስ መልክ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHERE AS, it has been found necessary to establish the strengthened entity that shall perform with integrated and organized manner of periodically rendered trainings and duties of education,study, research and rendering of the councelling service, that shall be conducted in this aspect, for leaders and professinals, that serve be appointed or assigned by different rural, as well as, city administrational levels;

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ /49/ ንዑስ አንቀፅ 3/1/ ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

NOW THEREFORE, the Council of the Amhara Region, pursuant to the powers vested in it under Article /49/, sub-article 3/1/ of the Revised National Regional Constitution, hereby proclamas this proclamation.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የአመራር አካዳሚ ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 221/2007 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

1. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

ሀ. "ሠልጣኝ" ማለት አካዳሚው ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚያወጣቸው መመዘኛዎች መሠረት ተመልምሎ በየትኛውም የስልጠና መርሀ-ግብር እንዲሳተፍ የተፈቀደለትና በስልጠና ላይ የሚገኝ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ነው፤

ለ. "አመራር" ማለት በክልሉ ውስጥ በሚገኙት የገጠርም ሆነ የከተማ አስተዳደር እርከኖች በታቀፉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በሀላፊነት ተሹሞ ወይም ተመድቦ የሚያገለግል ማንኛውም ሰው ሲሆን የብዙሀን ማህበራት እና የግሉን ዘርፍ መሪዎች ይጨምራል፤

ሐ. "ባለሙያ" ማለት በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም በግል ዘርፍ ተቋማት ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ በማገልገል ላይ ያለ ማንኛውም ሰው

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as "the Amhara National Regional State Leadership Academy Establishment and Powers and Duties Determination Proclamation No. 221/2014".

### 2. Definition

**1.** Unless the context otherwise requires, in this proclamation:

a. "Trainee" means any Natural person who are allowed to participate in any training action plan and elected with criteria to be issued by Academy, following this proclamation;

b. "Leadership " means any person serves as a head to be appointed or assigned in government sectors that are included in rural, as well as, city administrational levels in the Region; and, includes leaders of public associations and private sectors;

c. "Professional" means any person who is employeed or assigned and serves in government sectors, government development organizations or in private institutions in the region.

ነው፡፡

2. በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው ለሴት ጾታም እኩል ተፈጻሚ የሆናል፡፡

3. **<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በአካዳሚዉ ስር በተደራጁት የስራ ዘርፎችና በትምህርትም ሆነ በስልጠናው ተሳታፊዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ አመራር አካዳሚው መቋቋም፣ ዓላማ፣ ሥልጣንና አደረጃጀት</u>

4. **<u>ስለመቋቋምና ተጠሪነት</u>**

1. የአማራ ብሄራዊ ክልል አመራር አካዳሚ ከዚህ በኃላ "አካዳሚው" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለዉ የክልሉ መንግስት ከፍተኛ የትምህርት የስልጠናና የምርምር ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2. አካዳሚው በሙያ ስራ ረገድ የሚኖረው አስተዳደራዊና አካዳሚያዊ ነጻነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል፤
3. የአካዳሚዉ ዋና መስሪያ ቤት በባህርዳር ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ዉስጥ በሚገኙ ሌሎች ስፍራዎች ቅርንጫፍ ወይም ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችን ሊያደራጅ ይችላል፡፡

2. Any provision stipulated in masculine gender under this proclamation, shall also equally applicable for feminine gender.

3. **<u>Scope of Applicability</u>**

This proclamation shall be applicable on types of work organized herein under the Academy and education, as well as, trainees of training.

## <u>PART TWO</u>

## <u>Establishment, Objective, Power and Organization of the Academy</u>

4. **<u>Establishment and Accountability</u>**

1. The Amhara National Regional State Leadership Academy( herein after, referred to as " the Academy" is hereby established, as autonomous and having juridical personality of the Regional Government higher education, training and research institution by this proclamation;
2. Without prejudice to the administarional and economic freedom, the Academy shall be accountable to the Head of the National Regional State, with regard to professionalism;
3. The Head office of the Academy shall be in Bahair Dar Town; as deemed as necessary; it may organize a branch or coordinating offices in other places of the Region.

## 5. ዓላማዎች

አካዳሚው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ ዉስጥ በየአስተዳደር እርከኑ የአመራር ስፍራ ተሰጥቷቸው ህዝብን የሚያገለግሉ የስራ መሪዎችና ደጋፊ ሙያተኞች በአመራር ሣይንስ ረገድ ሰፊ ዕዉቀት የገበዩ፣ በክህሎት የተገነቡና በከፍተኛ ስነ-ምግባር የታነፁ ሆነዉ እንዲወጡ ደረጃዉን የጠበቀ የትምህርትና ስልጠና መስጠት፤
2. የዘርፉን ሽግግር የሚያቀላጥፉ ተተኪ አመራሮችንና ባለሙያዎችን በብቃትና በጥራት ማፍራት፤
3. የየደረጃዉን አመራር የላቀ ብቃትና የተወዳዳሪነት አቅም እንዲኖረው አድርጎ በማውጣት የክልሉንም ሆነ የሀገሪቱን ህዳሴ ጉዞ ቀጣይነት ከወዲሁ ማረጋገጥ፤
4. በጥናት፣ በምርምር፣ በምልከታና በትንተና ላይ የተመሰረቱና በአስተማማኝ ማስረጃዎች የተደገፉ ሳይንሳዊና ችግር ፈች ሃሳቦችን የሚያፈልቅና ለምልዓተ-ህዝቡ ተጠቃሚነት ሣይታክት የሚሰራ አመራር መገንባት፡፡

## 6. መርሆዎች

አካዳሚው ከዚህ በታች የተመለከቱትን መርሆዎች ተከትሎ ስራዎቹን ያከናውናል፡-

1. ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አመለካከትና አስተሳሰብ መያዝ፤
2. ሁልጊዜ መማር፣ መማማር እና መመራመር፤

## 5. Objectives

The Academy shall have the following objectives, pursuant to this proclamation:

1. To render a standardized education and training for leaders and support professionals who serve the public, rendered a leadership position with different administrational levels in the Region; to have a borad knowledge about management science, skillful and highly ethical;
2. To produce the next leaders and professionals with efficiency and quality, who speed up the transition of the Leadership Academy;
3. To ensure the regional, as well as, the country sustainability of renewal journey, by producing the different levels of leader, having a better efficiency and competitive capacity;
4. To produce a leader , who shall work with effort to the use of the whole people and generate sicentific and problem solver ideas , based on the study, research, observation and analysis and supported with reliable evidences;

## 6. Principles

The Academy shall carry out activities following indicated principles herein under;

1. To hold development and democratic outlook and thinking;
2. To learn,negotiate and discover always;

3. ክልሉ የተደራጀበትን ሕገ-መንግስታዊ ስርዓት ማክበርና ማስከበር፣
4. በብዝሃነት፣ በሕዝብ ወሳኝነትና ዘላቂ ተጠቃሚነት ማመን፤
5. የግልጽነትና የተጠያቂነት ስርዓትን ማስፈን፤
6. የለውጥ ፕሮግራሞችን ግንባር ቀደም ሆኖ ማራመድ፡፡

## 7. የአካዳሚው ሥልጣንና ተግባር

አካዳሚው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በሀገሪቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ዙሪያ የየደረጃውን አመራርና ፈፃሚ ሀይሎች በብቃትና በጥራት ለማፍራት የሚያስችሉና በዘመናዊ የጥናት፣ የምርምር፣ የምልከታ፣ የትንተና እና የሥርፀት ሥራዎች የተደገፉ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ትምህርትና ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ ለዚሁ የሚያገለግሉ ሞጁሎችን ያዘጋጃል፣ ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ያደራጃል፤
2. ክልላዊ እና ሀገር አቀፍ የልማት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ መርሆዎችንና ዓላማዎችን መነሻ በማድረግ ዝርዝር የትምህርትና የስልጠና መርሀ-ግብሮችን ይቀርፃል፣ በቦርዱ ሲፀድቁለትም በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

3. To respect and cause to respect constitutional system that the region is organaized;
4. To believe with diversity, public decisive and sustainably use;
5. To establish systems of transparency and accountabilty;
6. To lead programs of chanage ahead of others.

## 7. Power and Duty of the Academy

The Academy shall have the following particular powers and duties, pursuant to this proclamation:

1. Render the short, medium and long term education and trainings that enable to produce with efficiency and quality and supported with modern study, research, observation, analysis and create awareness on activities of each level leader and professionals with the countries policies and strategies; prepare modules that serve for trainings; and organize other similar educational materials.
2. Design particular educational and training action palns, starting from regional and country wise development policies, strategies, principles and objectives; cause to be effected on its approval by the board;

3. የሚሰጣቸውን የትምህርትና የስልጠና መርሀ-ግብሮች ተከታትለው ላጠናቀቁ እጩ ምሩቃን የምስክር ወረቀትና እንደ ተገቢነቱ በሀገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ሌሎች ተዛማጅ ህጎች መሠረት ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ ይሰጣል፤
4. የራሱን የትምህርትና ስልጠና አሰጣጥ በየጊዜው ለማሻሻልም ሆነ የክልሉን መንግስታዊ ተቋማት የማስፈፀም አቅም ለመገንባት የሚረዱ የጥናትና የምርምር ስራዎችን ያካሂዳል፤
5. ከመንግስታዊ መ/ቤቶች ወይም ተቋማት፣ ከመንግስት የልማት ድርጅቶችና ከግሉ ዘርፍ በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት በአመራር ፍልስፍናና በሥነ-ምግባር ግንባታ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችንና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
6. በየጊዜው የሚሰጣቸውን ትምህርትና ስልጠናዎች በተመለከተ የግምገማና የምዘና ሥርዓት ቀርጾ በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
7. በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች የሚያገለግሉ ባለሙያዎችን የሥራ አመራር ብቃት ለማጎልበትና ለማሳደግ የሚረዱ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ስልጠናዎችን ይነድፋል፣ ያሰለጥናል፣
8. በጥናትና ምርምር ስራዎች የተገኙ ውጤቶች ያሳትማል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤
9. ቦርዱ በሚያወጣቸው የምልመላ መስፈርቶች መሰረት ሰልጣኞችን ይቀበላል፣ የዕለት ተዕለት ግንባታቸውን በቅርብ ይከታተላል፤

3. Render certficate for those who completed the rendered educational and training action plans; and, as deemed as necessary, pursuant to other related laws of the Country's Higher Education Proclamation No. 650/2008, shall render Diploma or Degree;
4. Conduct studies and researches help to improve its own education and training rendering periodically, as well as, to promote execution capacity of the regional government institutions;
5. Render trainings and counceling services that emphasize on leadership philosopy and development of code of conduct, pursuant to request submmitted from government sectors or institutions, government development organizations and private sector;
6. cause to be implemented with regard to trainings that it renders periodically, designing the evaluation and assessment procedure;
7. Design the short and medium trainings that help to strengthen and promote management efficiency of professionals, in the regional government sectors; and shall train the trainees;
8. Publish and distribute results for users, found by study and research activities;
9. Receive trainees, pursuant to selection criteria that shall be set by the board; follow up their promotion closely;

10. በስሩ የተለያዩ የትምህርት፣ የስልጠና፣ የጥናትና የምርምር ክፍሎችን ያቋቁማል፣ የቤተ-መፃህፍትና የቤተ-ሙከራ አገልግሎቶችን ያደራጃል፣ ተፈላጊ ግብዓቶች እንዲሟሉላቸው ያደርጋል፤

11. ሰልጣኞች የተሰጣቸውን ስልጠና አጠናቀው ወደየስራቦታቸው ሲመለሱ የሚኖራቸውን አፈፃፀም በቅርብ ይከታተላል፣ የስልጠና ዉጤታማነት ጥናት ያካሂዳል፣ ግኝቱን በተመለከተ ለሚመለከተዉ አካል ሪፖርት ያደርጋል፣ ከዚሁ በመነሳት የተሻሉ የአሰራር ስልቶችን ይቀይሳል፤

12. የተለያዩ ትምህርታዊ ሴሚናሮችን፣ ወርክ ሾፖችን፣ ኮንፈረንሶችንና አውደ- ጥናቶችን ያዘጋጃል፣ ያካሂዳል፣ ጥሪ ሲደረግለትም በንደነዚህ ዓይነት መድረኮች ይሳተፋል፤

13. አቻዎቹ ከሆኑና ተቀራራቢ ዓላማ ካላቸው የክልልና የፌደራል መንግስት ተቋማት ጋር የስራ ግንኙነቶችን ይመሰርታል፣ በትብብር ስልጠና ይሰጣል፣ ከሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በዉጭ ሀገር ከሚገኙ መሰል የስልጠናና የምርምር ተቋማት ጋር ሊገናኝና ተሞክሮዎችን ሊለዋወጥ ይችላል፤

14. የሥራ አመራር ሥልጠና፣ የምክር አገልግሎትና የጥናት ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ገቢ የሚያገኝባቸዉን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እንደአስፈላጊነቱ ተመጣጣኝ ዋጋ ያስከፍላል፤

15. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ዉሎችን ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

16. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች

10. Establish different education, training, study and research departments under it; organize the library and laboratory services; cause to fulfill the necessary inputs;

11. Follow up closely the performance of trainees after training in jobs; conduct a research of training effectiveness; concerning to findings, it shall report to the pertinent body; and design better work procedures strating from it;

12. prepare and conduct different educational seminars, workshops, conferences and workshops; and participate on such type of forums when they are called;

13. Establish work relationship with the regional and federal government institutions, which are equal to it in status and having similar objectives; render training with collaboration; it may create relationship and interchange best practices with similar training and research institutions in foreign country, coincide with the country's foreign policy principles and objectives;

14. facilitate conditions that used to get revenue, by preparing management training, counceling service and the the study projects; as deemed as necessary, it cause to pay proportional for rendering serveces;

15. Own property , enter into contract, sue and be sued by its name;

16. Perform other related activities that are used to

ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

achieve its own objectives;

## 8. አደረጃጀት

አካዳሚዉ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1. የስራ አመራር ቦርድ፤
2. በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር፤
3. በቦርዱ አቅራቢነት በርዕሰ መስተዳደሩ የሚሾሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤
4. የአካዳሚዉ ጉባኤ፤
5. ብዛታቸዉ ለሥራዉ በሚኖራቸው አስፈላጊነት ላይ ተመስርቶ የሚወሰን የአካዳሚዉ የሥራ ክፍሎች፤
6. ለስራዉ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ድጋፍ ሰጭ ክፍሎች፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለአካዳሚዉ አካላት ውስጣዊ አወቃቀር፣ ተግባርና አሰራር

## 9. ስለ አካዳሚው የስራ አመራር ቦርድ መቋቋም፣ተጠሪነትና የአባላት ጥንቅር

1. የአካዳሚዉ የስራ አመራር ቦርድ ከዚህ በኃላ “ቦርዱ” እየተባለ የሚጠራ የአካዳሚው ከፍተኛ የስልጣን አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2. የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሆኖ ከሚከተሉት አባላት የተውጣጣ ይሆናል፡-

   ሀ.ርዕሰ መስተዳድሩ ወይም በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰየም የስራ ኃላፊ___ ___ሰብሳቢ

## 8. Organaization

The Academy shall have the following entities, pursuant to this proclamation:

1. Management Board;
2. One Director General, appointed with the Head of Regional Government;
3. Deputy Director Generals appointed with the Head of Gevernment, proposed with the Board;
4. Academic Commission;
5. The number of Academic departments shall be determined with their necessity for the activity;
6. Other support staffs, necessary for the activity.

## PART THREE

## Internal Organization, Duty and Procedure of the Bodies of Academy

## 9. Establishment, Duty and Procedure for the Management Board of the Academy

1. The management board of Academy /herein after called “ Board”/ is established as the higher power entity of the academy with this proclamation;
2. The Board shall be accountable to the Head of the Region, and shall have the following members:
   a. The Head of the Region or the Head of the office, nominated by the Head of the Region ...... chair person;

ለ. ይህንን አዋጅ መሠረት በማድረግ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሰየሙና ቁጥራቸው ከ5 ያልበለጠ የስራ ሀላፊዎች ____________________አባላት፤

ሐ. የአካዳሚዉ ዋና ዳይሬክተር________ አባልና ፀሃፊ፡፡

b. The Head of the offices that shall be nominated with the Head of the Government and not more than five in number, pursuant to this proclamation...........members

c. Director General of the Academy..... Member and secretary

## 10. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በአካዳሚዉ የትምህርት፣ የስልጠና፣ የምርምርና ስርፀት ጉዳዬች ላይ አጠቃላይ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ይወስናል፤
2. የአካዳሚዉን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ በቅርብ ይከታተላል፣ ተግባሩን በሚገባ ስለመወጣቱ ይቆጣጠራል፤
3. የአካዳሚውን አደረጃጀት፣ የስራ ዕቅድ፣ የአሰራር ሥርዓት ፕሮፖዛሎች መርምሮ ያፀድቃል፣ በዋና ዳይሬክተሩ ተዘጋጅተው የሚቀርቡለትን የውሳኔ ሀሳቦች እና ሪፖርቶች በየጊዜው ይገመግማል፣ ውሣኔዎችን ያሳልፋል፤
4. በአካዳሚው ተዘጋጅተው የሚቀርቡለትን ረቂቅ መመሪያዎች መርምሮ ያፀድቃል፣ አተገባበራቸውን በቅርብ ይከታተላል፤
5. የአካዳሚውን ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች በእጩነት አቅርቦ በርዕሰ መስተዳድሩ ያሾማል፤
6. የአካዳሚውን ኦዲተሮች ይሾማል፣ ክፍያቸውን ይወስናል፤

## 10. Powers and Duties of the Board

The Board shall have the following particular powers and duties, pursuant to this proclamation:

1. Determine general policy directions on the Academy education, training , research and the internalize issues;
2. Follow up general performance of the Academy closely; and supervise the accomplishment of its activity;
3. Approve by investigating the Academy organization, work plan and proposals of work procedure, periodically evaluate resolutions prepared and submmitted by Director General, and pass decisions;
4. Investigate and approve draft directives that shall be submitted, prepared by the Academy; follow up their implementation closely;
5. Submit the Academy Deputy Directors General as candidates,to be nominated by the Head of the Region;
6. Appoint the Academy Auditors and determine their payments;

7. ለአካዳሚው መሻሻልና ዕድገት የሚጠቅሙ የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
8. በአካዳሚዉ አማካኝነት ተዘጋጅተው የሚቀርቡለትን የትምህርት፣የስልጠናና የአቅም ግንባታ መርሀ-ግብሮች መርምሮ ያፀድቃል፤
9. የአካዳሚያዊና የአስተዳደር ሰራተኞች የሚተዳደሩበትን አጠቃላይ መመሪያ ያወጣል፣ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
10. ምክትል ዋና ዳይሬክተሮችን ሳይጨምር በዋና ዳይሬክተሩ ተመልምለው የሚቀርቡለትን የተለያዩ የስራ ዘርፎች ኃላፊዎችን ሹመት መርምሮ ያፀድቃል፣ ከኃላፊነት እንዲነሱ ያደርጋል፤
11. ለአካዳሚዉ መለያ የሚሆን አርማ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤
12. አካዳሚዉ ለሚሰጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች የሚጠየቁትን ክፍያዎች መጠን ይወስናል፤
13. የአካዳሚ ሰራተኞችን የደመወዝ ደረጃና ጥቅማጥቅሞች ይወስናል፣ እድገትና ሽልማቶችን መርምሮ ያፀድቃል፤
14. የአካዳሚው ዋና ዳይሬክተር በሚሰጠው ውሣኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ቢኖሩ እነዚህኑ መርምሮ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፤
15. የአካዳሚዉን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

7. Render counseling servces that are useful for the Academy improvement and promotion;
8. Investigate and approve the training and capacity building action plans, prepared and submitted in case of the Academy;
9. Issue general directives; that the Academy and administrational workers shall be governed; and follow up upon implementation;
10. Investigate and approve different sectors heads appointment, recruited and proposed with Diretor General, with the exception of Deputy Director Generals;
11. Cause to be prepared the emblem to differentiate the Academy;
12. Determine the amount of payments requested for different services that the academy shall render;
13. Determine the salary scale and benefits of the Academy workers ; investigate and approve promotion and prizes;
14. Investigate and render the final decision, if grievances and complains are submitted on decision, that the Academy Director General shall render;
15. Perform other related activities that help to achieve objectives of the Academy.

## 11. ስለ ቦርዱ የስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት

1. ቦርዱ በዓመት አራት ጊዜ መደበኛ ስብሰባዎችን ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤
2. የቦርዱ ምልዐተ-ጉባኤ የሚሆነው ከአባላቱ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ሲገኙ ይሆናል፤
3. የቦርዱ ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤
4. ከዚህ በላይ የሰፈሩት የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ጊዜና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 12. ስለ ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለቦርዱና ለርዕሰ መስተዳድሩ ሆኖ የአካዳሚው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጡት አጠቃላይ አቅጣጫዎች መሰረት የአካዳሚውን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የአካዳሚው ዋና ዳይሬክተር የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. የአካዳሚዉ ዓላማዎችና መሪ እሴቶች መከበራቸዉን ያረጋግጣል፤



## 11. Time of Meeting and Procedure of Rendering Resolution of the Board

1. The board shall conduct regular meeting four times a year. where as, as deemed as necessary, it may call urgent meeting at any time;
2. The quorum of the board shall be held, where members found more than half in the meeting;
3. Decisions of the board shall pass by majority vote; where as the vote is in tie, the chairperson shall have a decisive vote;
4. Without prejudice to the stipulated provisions of this Article here in above, the board may issue its own time of meeting and procedure of rendering resolutions directives;

## 12. Power and Duty of the Director General

1. The Director general shall be accountable to the Board and Head of the Region, and shall direct and coordinate activities of the Academy superiorly, pursuant to the general principles rendered with the board, as the general executive body of the Academy;
2. Without prejudice to the general provision stipulated under sub-article (1) of this Article, the director general of the Academy shall have the following particular powers and duties:

**a.** Ensure the Academy objectives and leading values to be respected;

ለ.በአካዳሚዉ አማካኝነት ለየርከኑ አመራሮችና ሙያተኞች የሚሰጡት ትምህርትና ስልጠናዎች በክልሉና በሀገሪቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ ያተኮሩ መሆናቸዉን ያረጋግጣል፤

b. Ensure the rendered education and trainings, for leaders and professionals by the Academy, focused on the Region and country's policies and strategies.

ሐ. አካዳሚዉ አግባብነት ካላቸዉ የአገር ዉስጥና የዉጭ አገር የትምህርት፣ የሥልጠናና የምርምር ተቋማት ጋር የስራ ግንኙነቶችን እንዲፈጥር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

d. Facilitate conditions for the Academy to create work relationship with pertinent body, in and out of the country of the education, training and research institutions;

መ.የአካዳሚዉን የትምህርት ክፍሎች አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት ቀርጾ ለቦርዱ በማቅረብ ያስገመግማል፣ ሲፀድቅለትም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

d. Design the Academy's educational departments organization and work procedure, and caue to be evaluated, by submitting to the board ; cause to be implemented upon approval;

ሠ. መማር-ማስተማርን፣ ምርምርንና ስልጠናን የሚያበረታታ ተቋማዊ አካባቢ እንዲፈጠር በትኩረት ይሰራል፣ ቀጣይነቱን የሚያረጋግጡ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

e. Perform with attention to be created institutional environment, that shall encourage teaching-learning process, research and training ; shall take measures to ensure its sustainability;

ረ. የአካዳሚዉ አበይት የትምህርት፣ የምርምርና የስልጠና ተግባራት የክልሉ መንግስት ቅድሚያ በሚሰጣቸዉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ላይ አተኩረው መከናወናቸውን በየጊዜው ይከታተላል፣ አካዳሚዉ የክልሉ አመራር የጥናትና ምርምር እንዲሁም የልማትና መልካም አስተዳደር አዳዲስ ሃሳብ ማመንጫ ማዕከል ሆኖ እንዲሰራ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

f. Follow up periodically the execusion of major education research and training activities of the Academy, focuses on policies and strategies that the regional government renders; facilitate conditions for the Academy that used to work as a new idea generating center of study and research of the regional leadership, as well as, the development and good governance;

ሰ. የአካዳሚዉን ተቋማዊ የደረጃ መለኪያከዎች ያዘጋጃል፣ የአስተዳደር ስራዎች በወጡት የደረጃ መለኪያዎች መሰረት መፈጸማቸዉን በትጋት ይከታተላል፤

g. Prepare the standard criteria of the Academic institution; and follow up attentively the administrational activities are executed, pursuant to the issued criteria of standard;

ሸ. በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የአካዳሚዉን የአስተዳደር ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ቀ. የአካዳሚዉን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የሥራ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የሥራና የበጀት መርሐ- ግብር ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድለትም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

በ. በአካዳሚው ስም የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሣቅሳል፤

ተ. አካዳሚዉ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ መርሀ-ግብር መሠረት ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ያደርጋል፤

ቸ. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች አካዳሚዉን ይወክላል፤

ኀ. የአካዳሚዉን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ነ. ለአካዳሚው ስራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከስልጣንና ተግባራቱ በከፊል ለአካዳሚው የበታች ስራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሰራተኞች በውክልና ሊያስተለልፍ ይችላል ፣

ኘ.በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ



h. Recruit and administer the Academic administration workers, pursuant to the regional civil service laws, regulations and directives;

i. Prepare the Academic short, medium and long term work plan, annual work and budget action plan; cause to be implemented upon approval;

j. Open book account and implement in the name of the Academy;

k.Cause to Expenditure finance, pursuant to the approved budget and work action plan of the Academy;

l. Represent the Academy in relation with the third parties;

m. Prepare and submit the performance and account reports of the Academy to the board;

n. May transfer partially from its powers and duties to the Academy lower officials and other workers, where it is necessary to speed up work of the Academy;

o. The board shall perform other related activities to be rendered.

13. ስለ አካዳሚዉ ምክትል ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር

1. አካዳሚዉ በቦርዱ አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾሙ ምክትል ዳይሬክተሮች የሚኖሩት ሲሆን ተጠሪነታቸው ለዋና ዳይሬክተሩ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፡-

ሀ. በሃላፊነት የሚረከቧቸውን የስራ ዘርፎች በበላይነት ይመራሉ፣ ያስተባብራሉ፤

ለ.በአካዳሚው ውስጥ ያስተምራሉ፣ ያሰለጥናሉ፤

ሐ. ዋና ዳይሬክተሩ ሃላፊነቱን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ በቅርብ ያማክራሉ፣ ያግዛሉ፤

መ. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተዉ የሚሰጧቸውን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናሉ፤

2. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ ከመካከላቸው በሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል ዳይሬክተር እርሱን ተክቶ ይሰራል፤

14. ስለ አካዳሚ ጉባኤ መቋቋም

1. ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተሩ የሆነ የአካዳሚ ጉባኤ ከዚህ በኃላ "ጉባኤው" እየተባለ የሚጠራ የአካዳሚው ጉባኤ ወይም ሴኔት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2. ጉባኤው ሰብሳቢውን ጨምሮ ቁጥራቸው በቦርዱ የሚወሰን አባላት ይኖሩታል፤ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

13. **Powers and Duties of the Deputy Directors of the Academy**

1. The Academy shall have deputy directors, proposed with the board and appointed by the Head of Government; they are accountable to the Director General, and shall have the following powers and duties, pursuant to this proclamation:

a. Direct and coordinate areas of work that they shall receive with responsibility superiorly;

b. Teach and train in the Academy;

c. Counsel and support closely the director general thatshall discharge its responsibility properly;

d. Perform other related activities that shall be rendered in isolation by the director general;

2. In the absence or inability of the director general, he or she senior in appointment deputy director shall replace and act on behalf of the director general;

14. **Establishment for the Commission of the Academy**

1. The Academic Commission, that shall be accountable to the Director General/herein after called "the Academy"/, the Academy's commission or senate is established with this proclamation;

2. The commission,shall have members determined their numbers with the board; including its chair person. The particulars shall be determined by the directives, that shall be issued for the implementation of this proclamation.

## 15. የጉባኤው ተግባርና ኃላፊነት

ጉባኤው የአካዳሚውን ትምህርትና ስልጠና ጉዳዮችን በሚመለከት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የአካዳሚውን የትምህርትና ስልጠና ካሌንደር ይወስናል፤
2. የአካዳሚውን የትምህርትና የስልጠና ፕሮግራሞችንና ሥርዓተ ትምህርት ይወስናል፣ የትምህርትና የስልጠና ዘርፎች የሚያካሂዱትን የጥናትና ምርምር ሥራወች ጥራትና አግባብነት ለማረጋገጥ እንዲችሉ ያደርጋል፤ አቅጣጫ ያስይዛል፤
3. የሰልጣኞችን አቀባበል፣ የትምህርትና ሥልጠና ደረጃ አወሳሰንን እና የዲሲፕሊን ጉዳዮችን በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መርምሮ ይወስናል፤
4. የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማ እና ዲግሪ የሚሰጥበትን አግባብ ይወስናል፤
5. የአካዳሚዉን ልዩ ልዩ የትምህርትና የስልጠና ፕሮግራሞች ያፀድቃል፡፡
6. በአካዳሚው የሚሰጠውን የትምህርትና የሥልጠና አግባብነትና ጥራት ማረጋገጫና የሰልጣኞች ምዘና ሥርዓትን ያወጣል፣ አጠቃላይ የመግቢያና የመውጫ ፈተና አሰጣጥንና ደረጃዎችን ይወስናል፤
7. በቦርዱ የሚሰጡ ፖሊሲወችን መሠረት በማድረግ የሰልጣኞች አስተዳደር፣ የአካዳሚው የትምህርትና ሥልጠና ነክ ጉዳዮች፣ የትምህርት ኃላፊዎች የምርጫ ሥነ-ስርዓት፣ የመምህራን ቅጥር፣ ዕድገት፣ ጥቅማ ጥቅም፣ ዲሲፕሊንና ደመወዝ በሚመለከት መመሪያ ያወጣል፤በቦርዱ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

## 15. Duty and Responsibility of the Commission

The commission shall have, the following duties and responsibilities, with regard to the education and training issues of the Academy:

1. Determine the education and training calendar of the Academy;
2. Determine the education and training programs and curriculum of the Academy; cause to enable to ensure its quality and appropriateness, that the education and training departments conducting a study and research activities; and guide directions;
3. Investigate and determine the submitted grievances concerning to the trainees acceptance, determination of the education and training standard and the discipline cases;
4. Determine appropriateness of rendering certificate, diploma and degree;
5. Approve different educational and training programs of the Academy;
6. Issue the education and the training appropriateness and quality assurance and the system of trainees assessment, that is rendered with the Academy; determine rendering and standards of General entrance and exit examination;
7. Pursuant to policies that shall be rendered with the board, the commission shall issue with regard to administration of trainees, the education and training issues, selection procedure of Heads of the education, recruitment, promotion, benefits , discipline and salary of the teachers;

8. በዳይሬክተሩ የሚመሩለትን ሌሎች ጉዳዮች መርምሮ ይወስናል፡፡

**16. ስለ ጉባኤው የስብሠባ ጊዜና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት**

ጉባኤው ተቀባይነት ያላቸውን መርሆዎች መሠረት በማድረግ የራሱን ውስጣዊ የስብሰባ ጊዜና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት ማስፈፀሚያ መመሪያ ያወጣል፡፡

**17. የአካዳሚው የሥራ ክፍሎች**

የአካዳሚዉ ልዩ ልዩ የትምህርትና ስልጠና ፣ የምርምር እና የአስተዳደር የስራ ክፍሎች ወይም ዘርፎች አመራር አካላት አደረጃጀት፣ ዝርዝር ተግባር እና አሰራር ቦርዱ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**18. ስለ በጀት**

የአካዳሚዉ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፡-

1. በክልሉ መንግሥት የሚመደብ በጀት፤
2. አካዳሚዉ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚሰበሰብ ክፍያ፤
3. ሌሎች ምንጮች ፡፡

**19. ስለ ሂሣብ መዛግብት አያያዝና ኦዲት**

1. አካዳሚው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፤
2. የአካዳሚው ሂሣብና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ መዛግብትና ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም ቦርዱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች



8. Investigate and determine other issues referred by the Director.

**16. The Meeting Time and Decision Making Procedure of the Commission**

Pursuant to principles that have an acceptance, the commission shall issue directives, that are necessary for the implementation of its own internal time of meeting and decision making procedure.

**17. Departments of the Academy**

The organization of leadership bodies, particular duties and procedure of different education and training, research and administrational departments or areas of of the Academy, shall be determined by directives that shall be issued with the board.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**18. Budget**

Budget of the Academy shall be found from the following sources:

1. Budget allocated by the Regional Government,
2. Payments To be collected, from rendered services by the Academy,
3. Other sources.

**19. Handling and Audit of the Book Accounts**

1. The Acadamy shall have complete and correct book accounts;
2. Book accounts and finance of the Academy, as well as, archieves and documents of property, shall be audited by Auditor General of the Region or auditors, nominated by the Board.

በየጊዜው ይመረመራሉ፡፡

## 20. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል ስራ አመራር ኢንስቲትዩት የተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 137/1998 ዓ.ም ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 21. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

በአዋጅ ቁጥር 137/1998 ዓ.ም ተቋቁሞ ሲሰራ የቆየው የስራ አመራር ኢንስቲትዩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ወደተቋቋመው የአመራር አካዳሚ ተላልፈዋል፡፡

## 22. ደንብ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 23. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ቦርዱ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 24. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባህር ዳር**

**ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ገዱ አንዳርጋቸው**

**የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዝደንት**

## 20. Repealed and Inapplicable Laws

1. The Amhara National Regional State Management Institute Establishment Proclamation No.137/2006 is repealed and replaced with this proclamation;
2. Any law, regulation, directives or customary practices, shall not be applicable on matters provided in this proclamation.

## 21. Transfer of Right and Duty

Rights and Duties of the Management Institute Establishment Proclamation No.137/2006, is transferred to the newly established Leadersip Academy, pursuant to this proclamation.

## 22. Power to Issue Regulation

The Council of the Regional Government may issue Regulation, which is necessary for the full implementation of this proclamation.

## 23. Power to Issue Directives

The Board may issue particular directives, that are necessary for the full implementation of provisions of this proclamation; and, regulations that shall be issued, pursuant to this proclamation.

## 24. Rffective Date

This proclamation shall come into force as of its publication date in the Zikre-Hig Gazzettee of the Regional Government.

**Done at Bahir Dar,**

**This 7th day of November , 2014**

**Gedu Andargachew**

**President of the Amhara National Region**